


ተቀባይ ፡- ዲበኩሉ (ባሕር ማዶ)

ላኪ፡- የአራዳ ልጆች (ከአራዳ)

## ይድረስ ለዲበኩሉ፡-

ወዳጃችን ዲበ! ሠላምና ጤና ካንተ ጋር ይሁኑ! ለመሆኑ እንደምን ከርመሃል? እኛስ አለን - እንዳለን!። ክብር ይመሥገን ለፈጣሪ እያልን።

ዲበ! በዚህ መልዕክታችን ውስጥ የፈረንጅ አምላኩ የተቃውሞ ድምጽ አይገኝም። እንዳውም በመልዕክታችን ቆመው ካጨበጨቡት አንዱ ፈረንጅ አምላኩ ነው። እነ ኒቂሴም ቢሆኑ ቆመው ያስመዘገቡት አቤቱታ የለም። ብቻ ባለህበት ደህና ሁንልን ነው ያሉት። አይናቸው እንባ እያቀረረ። የነሽኩርና ዘበርጋም ስለ ዓለም ኢኮኖሚ መቅለጥ፤ ስለ ስኳርና ዘይት ዋጋ እንጦጦ ላይ መውጣት ያቀረቡት ትንታኔና ብታኔ የለም።

ከስድስት ኪሎ እስከ ፍራሽ-ተራ፤ ከመተባበር እስከ "አስጎሪ" ጠጅ ቤት፤ ከታክሲ ወያላዎች እስከ ዶሮ ማነቂያ ኮማሪቶች፡ በጥቅሉ በቅርብም በሩቅም የሚያውቁህ ወዳጆችህ ሁሉ፡- በአንድ ልብ በአንድ ልሣን ይህ መልዕክታችን በአስቸኳይ ይደርስህ ዘንድ ተስማምተን ድፍን አራዳ ያጨበጨበለትን ቃላችንን አስተማሪ አለሙ በጥሁፍ እንዲሰድልህ አድርገናል።

**እንሆ መልዕክታችን፡-**

ወዳጃችን ዲበ! መቼም አራዳ ላይ ከሁነኛ ምንጮች የማንሰማው ፤ አቅም በፈቀደ ከምናነበው ጋዜጣና መጽሄት የማናገኘው መረጃ የለም። በተለይ ስለናንተ! ስለ ዲያስፖራው እንቅስቃሴ ።

በአንድ ወገን፡- ጦቢያን ብላችሁ፤ እኛን ብላችሁ፤ ብርቱካንን ብላችሁ፤ አዱ-ገነት ላይ የተተከለው የግፈኞች አምባገነን አገዛዝ እንዲያከትም፤ የትንሣኤ ጦቢያ ችቦ እንዲለኮስ ፤ የተበተኑ ቡቃዮችም እንዲሰባሰቡ ፤ አንድ ሃገር አንድ ህዝብ ብላችሁ ሌት ተቀን የምትሠሩ የፈረንጅ ሃገር ወገኖቻችን መኖራችሁን ስንረዳ አለኝታነታችሁና ወገናዊ ፍቅራችሁ ውቂያኖስ ሰንጥቆ አድማስ ዘልቆ የተስፋ ምርኩዛችን ሆኗል። ለእናንተ ለባህር ማዶ ጮራዎቻችን ፅናቱን ይስጣችሁ!! እኛም አናሳፍራችሁም።

በሌላ ወገን ደግሞ፡- አብላጫ አሃዝ ያላችሁ የፈረንጁ አገር ወገኖቻችን በሃገራችሁ ዋይታና በወገናችሁ ሰቆቃ ጉዳይ ላይ እንደ መቃብር የከበደው ዝምታችሁ በእጅጉ አሳስቦናል። ቅርም አሰኝቶናል። የማይጨበጡትና ትርጉም ያጣንባቸው የአንዳንዶቻችሁ ተግባራትም ክፉኛ አሳዝነውናል። እንሆ ቅሬታዎቻችንን አንዷ በአንዷ ዘርዝረናል፡-

ዲበ፡- ለመሆኑ ከሣምንት ሣምንት የምታዥጎደጉዱት መግለጫ ምንድነው? የሚገልጠውስ ምንድነው? እስቲ ንገሩን። መቼም ለናንተ ነው እንዳትሉንና በሣቅ ሲቃ እንዳንሞት። ደግሞ የግጥሙስ ጋጋታ ምንድነው? "ፍየሉ ያለው እዚህ ቅዝምዝሙ ወዲያ" አሉ እትዬ አቻሜ።

እና እባካችሁ ግጥም አታብዙ። በደላችንን በግጥም ለማስተጋባት ግዜ አታባክኑ። እየደረሰብን ያለው ግፍና መከራ:- በመግለጫና በግጥም ወጌሽነት ታሽቶ የሚጠገን አለመሆኑን ተረዱ። ካቻምናም አምናም ሆነ ዘንድሮ :- እየሞትን እየታሰርን ፤ እየተደበደብን ፤ እየተሰቃየን ነው! ።

ለመሆኑ በአራት ኪሎዎቹ አምባ ገነነኖች ጥይት ሣንረሸን፤ ወህኒ ሳንማቅቅ፤ ቤት ንብረታችን ሳይወረስ፤ሳይፈርስ፤ ከት/ቤትና ከሥራ ሳንባረር፤ሳንፈናቀል፤ ያለፍንበት ዘመን አለን? የግፍ-ፅዋው ሞልቶ ሲፈስ፤ ከዳር እዳር ተጠራርተን፤ በአንዲት ባንዲራ ሥር አንድ ሆነን፤ እስከ አፍንጫኛው ከታጠቀ ሀገር ሻጭ፤ ታሪክ ከሃዲ ፤ መሠሪ ፤ ህዝብ አናቋሪ....ጋር በባዶ እጃችን ተናንቀን አልሞትናም? ስንትስ ግዜ አልታሠርንም? አሁንስ ቢሆን እየታሰርን እየሞትን አይደለም ያለነው? ታዲያ ለምንድነው? ትከሻን ለሸክም የተፈጠረ፤ ህሊናችን በፍቅረ ነዋይ የታወረ፤ በአድርባይነት የተሸመደመደን.......... ይመስል:- አንዴ በግጥም አንዴ በመግለጫ በደላችንን እየዘረዘራችሁ የምታጨናንቁን? እናም እየደረሰብን ያለውን ግፍና መከራ:- ከናንተ ግጥም በበለጠ በውስጡ ያለነው አሳምረን እናውቀዋለንና በግጥምና በመግለጫ ግዜ አታጥፉ። ግጥም ሲበዛም ሃሞት ያፈሳል። መግለጫም ማብዛት መመጻደቅ ነው።

አየህ ዲበ:- እኛን የቸገረን ጃንጥላ ነው። የናፈቀን ጃንጥላ ነው!። በጸሎትም ሆነ በስለት ልናገኝ ያልቻልነው ጃንጥላ ነው። ክረምት ከበጋ የሚያዘልቀን ጃንጥላ!። የሃምሌ ዶፉ ሳይወርድ፤ ገና ደመናው ሲያስገመግምና ማካፋት ሲጀምር ተሸንቁሮ የማያፈስ ፤ ያማያርስ ፤ ያማያረሰርስ ፤ አስተማማኝ ጃንጥላ!። የበጋው ሃሩር ሳይጠነክር፤ ሳይገር፤ ገና በማለዳው ጸሃይ ግሎ የማይበሳ ዣንጥላ!።

ታዲያ እንዲህ ያለ ጃንጥላ ከየት ይገኛል? እንጂማ ትናንሽ ጥላዎች መች ጠፉ። ግና እንኳን ለኛ ሊተርፉ ለራሳቸውም አልሆኑ።

እና :- ስለ ወላዲት አምላክ ብላችሁ ጦቢያን አቀፍ ጃንጥላ ካልሆነ፤ በየቅዬው ትናንሽ ጥላ ተከልላችሁ አትጥሩን። ልንደርስላችሁ ነው ብላችሁ አትላኩብን። ለመሆኑ እናንተ በነፍስ ወከፍ ጥላ ይዛችሁ በቆማችሁ ቁጥር የእኛን አንድነት እየገዘገዛቹሁ ፤ የጠላቶቻችንን ክንድ እያፈረጠማችሁ ፤የግፍ-ዘመኑን እያራዘማችሁ መሆኑን ስለምን መረዳት ተሳናችሁ?

እስኪ አስቡት:-እነሱ ከበሯቸውን እየደለቁ አራዳን አፍነው በመዳፋቸው ውስጥ ካደረገጓትና ካስገበሯት ወዲህ የተወለዱ ሕጻናት ዛሬ ለአቅመ አዳም/ሔዋን ደርሰዋል። ዘመኑ ቀላል አይደለም። ታዲያ:- እኛ የጦቢያ ልጆች በዚህ ሁሉ ዘመን ውስጥ እንዴት አንድ አስተማማኝ ጃንጥላ እንጣ? አያሳፍርም? አያስቆጭም? አያንገበግብም? እኮ እንዴት ነው ጦቢያ የሚታደጋት ክንድ ያጣችው?

አቤቱ ጦቢያ ሆይ! ለክብርሽና ለአንድነትሽ ጃንጥላሽን ያቆሙ ልጆችሽ ከወዴት አሉ? እስከመቼስ እጆችሽን ወደ እግዚአብሄር ዘርግተሽ ትጸልያለሽ? ያንቺ ሙሴ ከተራራ የሚወርደው መቼ ይሆን? ኤሎሄ! ኤሎሄ! አባት ሆይ ጦቢያን ምነው ረሳሃት?

ወዳጆችን ዲበ:- ለመሆኑ ሃገርን መውደድ፤ ወገንን ማፍቀር ማለት በፈረንጅ ሃገር አማርኛ ትርጉሙ ምንድን ነው? በስድስት ወር ወይም በአመት አንዴ ከሞትን ወይም ከታሰርን በኋላ በታላላቅ ከተሞች አደባባይ ላይ ባንዲራ ይዞና ባንዲራ ለብሶ መጮህ ብቻ ነውን? ደግሞ እንደምንሰማውና እንደምናየው ከሠላማዊ ሰልፈኛው መካከል ፤ ዱቤ-ከልል ኮፍያና ጥቁር መነጽር አድርጎ ከሜራ እየሸሸ የሚጮህው ይበዛል።

አደባባይ የምትወጡት በኛ ላይ እየደረሰ ያለውን በደል ለሌላው ዓለም ለማስገንዘብና ተቃውሟችሁን ለመግለጽ ከሆነ እራስን መደበቅና ካሜራ መሸሽ ለምን አስፈለገ? የሚል ነው የኛ ጥያቄ።

እኛ ደረታችንን ገልብጠን አደባባይ እየወጣን፤ በድንጋይና በዱላ ከግፈኞች ጋር ስንተናነቅ፤ እናንተ በፈረንጅ አገር እየኖራችሁ የኛን ጩሀት ለማስተጋባት ፊታችሁን መሸፈን ምን የሚሉት ነገር ነው? እያልን ዘወትር በግርምት

ማውራታችን አልቀረም።በኛ እምነት ፊታቸውን እየሸፈኑ አደባባይ ከሚወጡት ይልቅ አንደኛውን ፈረንጅ ሆነናል ብለው ከቶውንም ስለ ጦቢያዊነታቸውም ሆነ ስለ ጦቢያ ማሰብ ያቆሙት በድኖች ይሻላሉ።ለይቶላቸዋላ! እናም ፊት ሸፍኖ አደባባይ ወጥቶ ከመጮህ፦ እንደነሱ አልሰማንም! አላየንም! ብሎ መቀመጥ ይሻላል።

ወዳጆችን ዲበ ሆይ ፦ እንነሆ እንደካቻምናውና አምና ሁሉ ዘንድሮም ጦቢያን ውጋት ወጥሮ ይዟታል፡፡አዱ-ገነትም ሲቃ ላይ ነች። ሁሌም ትንፋሽ እንዳጠራትናት አራዳ!። ሁሌም እዳቃሰተች ናት ሸገር! ሁሌም እንዳተኮሰች። አራዳ ስታተኩስ ድፍን ጦቢያ ትግላለች፡፡ አዱ ገነትን ሲበራዳት ድፍን ጦቢያ ውርጭ ይመታታል።

የአራት ኪሎ ቲያትረኞች ስንትና ስንት ዓመት የጀመሩት ቲያትር መጋረጃው እንዳይዘጋ፤ ቲያትሩም እንዳያበቃ፤ ምርጫ ውጡ ፤ ድምጽ ስጡ ብለውናል። ምርጫውም በግንቦት ነው ብለዋል።

ግንቦት ደግሞ አዲስ አበባን ጉሮሮዋን አንቀው ድፍን ጦቢያን መርገጥ የጀመሩበት የንግርት ወራቸው ነው።በግንቦት ለሥልጣን-ዛራቸው መስዋዕት ያቀርባሉ፡፡ ጦቢያን ያሉ ፤ የጦቢያ ልጆች በአደባባይ፤ በጠራራ ጸሃይ ለመስዋዕት የሚዳረጉት በግንቦት ወር ነው።

እንደለመዱት ዘንድሮም ታጥቀው ተነስተዋል። የቲያትሩን አጋር ተዋንያኖች የዲሞክራሲያዊ ምርጫ - ካባ አልብሰው እነሱም የበግ ለምድ ደርበው ኑና አጨብጭቡ ሆ! በሉ እያሉ ይጠሩናል፡፡ የፈረደብንን የጦቢያን ቡቃዮች።

ለጸሃፊ-ተውኔቱ ጸልዩ ዕድሜውንም ያርዝመው ብላችሁ መርቁ ይሉናል። ካባ ለዋዋጮቹ ፤ አፋሽ አጎንባሾቹ የቲያትሩ ተዋንያኖችና የጸሃፊ-ተውኔቱ ደቀ-መዝሙሮች።

በአንድ እጃቸው ጠመንጃ በሌላ እጃችቸው ዳቦ ይዘው ነው ምረጡ የሚሉን። ዳቦ ብንመርጥ በጠመንጃው ግንባራችንን ይሉናል። ጠመንጃውን ብንመረጥ፤ ዳቦውንም ሳናገኝ በራሳችን ላይ"**ይሙት-በቃ**" መፍረዳችን ነው።

እንግዲህ ምን ምርጫ አለን? አሻፈረን ማን ይፈራል ሞት..! ከማለት በስተቀር? ሞትም እንደሁ ሞተን አይተነዋል። እስርም እንደሁ ወህኒ ማቀናል። ቤታችን ነው።

ከወዲህ ማዶ ደግሞ እኛን ያሉ፤ ጦቢያን ያሉ፡ አይዟችሁ ይሉናል።የምፀትና የሰቆቃ፤ የበቀልና የጥላቻ ቲያትር ይብቃ!፤ በተስፋይቱ ምድር ተስፋ ያንሰራራ!፤ ሠላም ይውረድ! ለሁሉም ይዳረስ! ረሃብ ይብቃ! ጎጠኝነት ይብቃ!ሰባዊ መብት ይከበር! ነጻነት ይኑር! ትንሣኤ ለጦቢያ ይሁን!።...የሚሉ ስለ ጦቢያ ብለው፤ ስለኛ ብለው፤ ማህበር ያቆሙ፤ ጽዋ ያንሱ፤ ወገኖች እንሆ ዘንድሮም ተነስተዋል።

እነኚህ በየመገናኛ ብዙሃን ቀርበው እኛን "ካልመረጣችሁ ዋላችሁ!" እያሉ አይዝቱብንም። ጣታቸውን ቀስረው አያስፈራሩንም። ይልቁንም የአምባ ገነኖች ድራማ የሚያከትምበትን አዲስ መድረክ አቁመው ፤ መድረኩን መድረካችን እንድናደርግና ትዕይንቱንም አብረናቸው እንድተውን መጋረጃውንም አብረን እንድንዘጋ ...ጋብዘውናል።

አየህ ዲበ፦ እነኚህ ብርትኳናችንን ያስታውሱናል። ፍርደ ገምድሎች ቀጥፈው ሊያሚሽሿት ታጠቀው የተነሱባትን፡ የኛዋን ብርትኳን!።

አዎ ብርትኳናችን "**ሃዘኔም ድሌም ከናንተ ጋር ነው፤ሞቴም ሽረቴም በጦቢያ ላይ ከጦቢያ ጋር ነው።የሰጠኋችሁ ቃሌ አይታጠፍም ።ስለ ቃሌ የከፈላችሁት ዋጋም አይመክንም**"ብላለች ገና በጠዋቱ ብርትኳን የኛይቱ!

ባለ ቅኔው ሎሬት ጸጋዬ፦ መይሳው ካሣን ከመቃብር ቀስቅሶ ቁጭቱን እንዲናገር በስሙ ባዘጋጀለት ተውኔት ላይ፡-የጀግናው የአንድ ለናቱ መንፈስ፦

አየሽ አንቺ እማማ ኢትዮጵያ! አየሽ አንቺ እናት ዓለም!

ቃል-የዕምነት ዕዳ ነው እንጂ የእናት አባት እኮ አይደለም! እንዳለው በያኔው የግንቦት ምርጫ ስለ ሞትነው ስለተጋዝነው፤ ቃሏን ጠብቃ ቃሏን አክብራ፤ ቃል-የእምነት ዕዳ ነው ብላ! ስለ ቃላችን ስለ ቃሏ፡፤ በአፓርታይድ እንደተጋዘው እንደ ማንዴላ፤ እሥር የተከረመችውን የነጻነት አርማችንን ብርትኳንን ያስታውሱናል እነኚህ ያሁኖቹ።

እነኚህ ጠመንጃም ዳቦም አልያዙም፡፤ እነዚህ በአንድ እጃቸው ሚዛን በሌላ እጃቸው አንዳች የሚያክል ጥራዝ ይዘው ነው ለግንቦቱ ትንንቅ የጠሩን።በሚዛኑ የምትመዝኑት እናተው ናችሁ ብለውናል።ተመዛኞቹ ደግሞ ቲያትረኞቹና እነሱ መሆናቸው ነው። ጥራዙስ?...ጥራዙ ደግሞ፤ እርሻዊ፤ፋብሪካዊ፤ መንገዳዊ፤ጤናዊ፤ ትምህርታዊ፤ወታደራዊ፤....ወዘተ ፕሮግራማችን ነው ይላሉ፡፤ እኛስ የታከተን ይሄ ፕሮግራም የሚባል ነገር ነው።ፕሮግራምና የድርጅቶች ጋጋታ፤ የድርጅቶች እንቢልታ፡፡

የሆኖው ሆኖ እነኚህ መድረክ አቁመው ወደ መድረኩ የወጡት ስብጥርጥራቸውም ሆነ ንግግራቸው አንጀታችን ጠብ ማለቱን አንደብቅህም።ከሁሉ ንግግራቸው ቀልባችንን የወሰደው ደግሞ፤ በግፍ የተዘረፍነውን አንጡራ ንብረታችንን "የአሠብ ወደብን" እናስመልሳለን ብለው አደባባይ ወጥተው ማወጃቸው ነው። መቼም እንዴት አንጀታችን ቅቤ እንደጠጣ ልንገልጽልህ  አንችልም።

ዲቦ፡- በኛ በኩል አሰብን ብቻ ሳይሆን ለባዕዳን የተቸበቸበውንና በመቸብቸብ ላይ ያለውን መሬታችንንም ፈርማቸውን ቀደን ውሉን እናፈርሳለን እንዲሉን እንፈልጋለን። ደግሞ አይቀርም። አሰብን ማስመለሳችን መሬታችንን ለባለመሬቱ ማስረከባችን አይቀሬ ነው፡፤

ወዳጃችን ዲቦ፡- ያም ሆነ ይህ ለግንቦቱ ምርጫ ያለን አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው። የጠላቶቻችንን ቆሸት እንድናደብን እግዚአብሄር ከፈቀደም ...ትግል፤ ጸሎታችን ከሠመረ፤ መቼም ቢሆን ተስፋ አንቆርጥም። እኛን ብለው፤ ጦቢያን ብለው፤ ብርትኳናችንን ብለው የተነሱትን እንመርጣለን።አዎ ያለ ጥርጥር የምንመርጠው እነሱን ነው።

እናም! ዘንድሮም እንደ 97 ሁሉ እንደጉንዳን ተመን ለምርጫ እንወጣለን። ጠመንጃቸውን ዘንድሮም እንደማንፈራ፤ እግረ ሙቃቸው ዘንድሮም ሸብቦ እንደማያስቀረን እናሳያቸዋለን። ለአራት ኪሎዎቹ አምባ ገነን ቲያትረኞች ።

መርጣችኋቸው ለድል ቢበቁና በመንግስትነት ቢቆሙ፡- ምን ይፈጥራሉ..? ምን ይሰራሉ..? ብላችሁ አትጠይቁን።ስለዚህ ጥያቄ አሁን ማሰብም ሆነ መተንበይ አንፈልግም።ያልጠገገ ቁስል አለብንና ያመረቅዛል።ከመረቀዘ ያመናል።እኛ ደግሞ በካቻምናው በሽታ ዘንድሮም መታመም አንፈልግም።

ዘንድሮም ምርጫ ነው። ጠመንጃና ዳቦ ይዘው ምረጡን የሚሉንን አንመርጥም። በፈቃዳችን እንደማንመርጣቸው ዘንድሮም እንዲያውቁት ስለምንፈልግ እኛን ያሉትን እኛን የመሰሉትን እንመርጣለን።ስለዚህ በምርጫው ስለመሳተፋችን አሉታዊ አዎንታዊ እያላችሁ በቁና ሙሉ ትንታኔ አታድክሙን።

ወዳጃችን ዲቦ!፡- እንግዲህ በወርሃ ግንቦት፤ " **በምድረ-ጦቢያ ልጆቿ በጠራራ ፀሃይ ተረሸኑ...በካሚዮኖች እየተጫኑም ወደ እስር ቤት ተጋዙ...**" የሚል ዜና በፈንጅ ሃገር ከፈረንጅ የዜና አውታሮች ብትሰሙ ወይም በቴሌቪዥን ስቃይና ሞታችንን ብታዩ በሮቻችሁን ዘግታችሁ አታልቅሱልን።ከንፈራችሁን እየመጠጣችሁ አትዘኑልን። በመግለጫም አትግለጡልን፡ ግጥምም አትግጠሙልን።

እኛን ከወደዳችሁ፤ ግፈኞችን ከታቃወማችሁ፤ ጦቢያን ታፈቀራችሁ፤ ብርትኳንን ካላችሁ፤ በየምትኖሩበት የፈረንጅ ሃገር በነቂስ ወጥታችሁ በፈረንጅ አደባባዮች ሁሉ ትመሙ!።

ለሠዓታት ሳይሆን ለቀናት ዓለም አንቀጥቅጧት ፡፡ አውሮፓን አጨናንቋት!፡፡አሜሪካን አጥለቅልቋት!፡፡አውስትራሊያን አናውጧት!፡፡እጅ ለእጅ ተይይዛችሁ በተባበረ ነጎድጓዳዊ ድምጽ **"ጦቢያ ላይ የሰፈነው ግፍና መከራ ይብቃ!"** ብላችሁ ዘምሩ፡፡ ተጣሩ!፡፡ ይህ ነው መልዕክታችን፡- በፈረንጅ ሃገር ለከተመው ወገናችን፡፡

ወዳጃችን ዲበ! እንሆ መልዕክታችንን አንዳችም ሳትቀንስ አንዳችም ሳታክል ታደርስልን ዘንድ አደራ ብለንሃል፡፡ ባልህበት ሠላም ሁንልን፡፡

ዘወትር የሚናፍቁህ ጓዶችህ፡- የአራዳ ልጆች !

ከአራዳ